

# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++
# የዕለት እንጀራ

[፫፻፷፩ኛው እንጀራ] ጥር ፴ ፳፻፪



”ዘመቻ ነፍስ” - የተቀደሰው ታላቁ የጌታ ጾም ነገ ይገባል። ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር በንስሐና በቁርባን የምንቀርብበት ወራት ይሆንልን ዘንድ በመንፈስ እንዘጋጅ፡፡

ዋጋችሁ
በሰማያት
ታላቅ
ነውና
ደስ ይበላችሁ።

ማቴዎስ ፭:፲፪

## ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ፥ እርሱንም በማምለክ ደስ ይበላችሁ። እግዚአብሔር እንዳይቈጣ ጥበብን አጽንታችህ ያዙ።

መዝሙር ፪፥፲፩

ሁልጊዜ
በጌታ
ደስ ይበላችሁ፤
ደግሜ እላለሁ፥
ደስ ይበላችሁ።

ፊልጵስዩስ ፬:፬

## በዚህ ቀን ከሚታሰቡት መካከል

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት

## ለማወቅና ለማድረግ

ከነገ ጀምሮ ዐቢይ ጾም ነው። ጾሙ ፶፭ ቀናት ሲይዝ እነዚህም በቅደም ተከተል፤

፩) ጾመ ሕርቃል (ሙሴኒ) - ፯ቀን
፪) የጌታችን ጾም (ጾመ ኢየሱስ) - ፵ ቀን
፫) ሰሙነ ሕማማት - ፰ ቀን ናቸው።

ዐቢይ ጾም የየራሳቸው መጠሪያና ምክንያት ባላቸው በ፰ ሳምንታት (ከእሁድ እስከ ቅዳሜ) ይከፈላል። እነዚህም ከዛሬ ጀምሮ ዘወረደ፤ ከዛ ቅድስት ፤ከዛ ምኩራብ ፤ከዛ መጻጉዕ ፤ከዛ ደብረ ዘይት፤ ከዛ ገብር ኄር ፤ከዛ ኒቆዲሞስ፤ ከዛ ሆሳዕና (ሰሙነ ሕማማት የሚጀምርበት)።

ዘወረደ - ከጌታችን በቀር ከስማይ የወረደ(የመጣ) ወደሰማይም በሥልጣኑ የሚወጣ የለም።